# በሕዝብ ትግል ላይ ዉሃ ለመቸለስ እየጣሩ የሚገኙ አድርባዮችንና የሕዝብ አደራ በሌዎችን ቸል ማለት አይገባም

*በሰሜን አሜሪካ ከደቡብ ሀብረት የተሃድሶ ኮሚቴ የተሠጠ መግለጫ*

ሠፊዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦቱ 1997 ምርጫ በነቂስ ወጥቶ የሚያምናቸውንና በትክክል ያስተዳድሩኛል ብሎ ያላቸዉን መሪዎቹን መርጦ ሲያበቃ በአንጻሩ ደግሞ የህወሃት/ኢህአዴግ መንግሥትን በቃሃኝ፡ ከአሁን በኋላ አትገዛኝም ብሎ በሠለጠነ መንገድ በምርጫ ሳጥን ድምፅ ማሰናበቱ ሁሉም የሚያዉቀዉ ሃቅ ነው። ሆኖም ከምርጫዉ ማግስት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሉ የተጎናፀፈውን የመምረጥ መብት ተጠቅሞ የፈለጋቸዉንና ያመነባቸዉን መሪዎቹን በመምረጡ ብቻ ቅጣት ተፈርዶበት በአረመኔዉ የመለስ መንግሥት የግፍና የመከራ ፅዋ እየተጋተ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ያስተዳድሩኛል ብሎ የመረጣቸዉ መሪዎቹም በግፈኞች እስር ቤት በመማቀቅ ላይ ይገኛሉ። ከአብራኩ የወጡ ወጣት ፤ ፍሬና ቀንበጥ ልጆቹ በአረመኔዉ የአጋአዚ ጦር ጥይት ግንባራቸዉን እየተመቱ ወድቀዋል ፤ ቁጥራቸዉ በዉል የማይታወቅ ደግሞ በየበረሃዎቹ ካምፖች ታጉረዉ ደብዛቸዉ ጠፍቶና አስተዋሽ አጥተዉ ቁም ስቅያቸዉን እያዩና እየተንገላቱ ይገኛሉ። የሕዝብ ጀሮና አንደበት ሆነዉ ሲያገለግሉ የነበሩ ጋዜጠኞች እስር ቤት ተወርዉረዉ ፍዳቸዉን እያዩ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ ዛሬ ሀገሪቱ ወደ እስር ቤትና የማጎሪያ ካምፕ ተለውጣ ባለችበትና ከግንቦቱ 1997 ምርጫ ማግሥት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፈጥሯዊ መብት በህገወጥ አዋጅና በጠመንጃ አፈሙዝ ተገድቦ የሀገሪቱ ዜጎች ከዚህ የግዞት ኑሮ ለመላቀቅ በየአቅጣጫዉ ትግሉን አፋፍመው በሚገኙበት ሁኔታ አድርባዮችና የሕዝብ አደራ በል የሆኑ “የተቃዋሚ የፓርላማ አባላት” ተብዬዎች በምድረ አሜሪካ እየተዘዋወሩ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት ተዘርግቷል ፤ ዴሞክራሲ ሂደት ነዉና ጊዜ ሊሠጠዉ ይገባል ፤ የተያያዝነዉ አቅጣጫ ትክክለኛ አቅጣጫ ነዉ ፤ ፓርላማ መግባታችን ትክክልና በሕዝባችን የተደገፈ ነዉ ወዘተ... በማለት የመለስን አምባገነናዊ መንግስት ፓርላማ ገብተዉ ህጋዊ ሽፋን እንደሰጡትና ነፍስ እንደዘሩለት ሁሉ አሁን ደግሞ ሊያጠናክሩትና ሊያደላድሉት የማምታት ዘመቻና ፕሮፓጋንዳ እየነዙ ይገኛሉ።

በኛ እምነት የዴሞክራሲ ሥርዓት ወይም የዴሞክራሲ ሂደት የሚባል ነገር ጨርሶ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የለም። መለስና አበሮቹ ለአስራ አራት አመታት በደሞክራሲ ስም የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲረግጡና ሲገዙ ቆይተዉ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ ግን የደሞክራሲ ጭንብላቸዉን አዉልቀዉ በመጣል የለየላቸዉ አምባገነን ሆነዋል። ስለዝህ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ ሥርዓት አንድ ግለሰብ ከጥቂት ግብረአበሮቹ ጋር በመተባበር በጠመንጃ ኃይል የኢትዮጵያን ሕዝብ አፍኖ እየገዛ ያለበት የለየለት የአምባገነንና የፖሊስ ሥርዓት መንግሥት ነዉ። በአንፃሩ ሲታይ የነበረዉም የዴሞክራሲ ጭላንጭል ደብዛዉ ጠፍቶ ነጻ ፕሬስ ተዘግቶ የግል ጋዜጣ አዘጋጆችና ጋዜጠኞች በእስር ቤት ታጉረዉ እየተጉላሉ ባሉበትና የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪዎችና የቁርጥ ቀን ልጆች ዘብጠያ ተወርዉረዉ ባለበት ሁኔታ የደሞክራሲ ሥርዓት አለ ብሎ መናገር “ጅብ በበላበት ይጮሃል” የሚባለዉን ከማሳየትና የአድርባዮችን ማንነት ግልፅ አድርጎ ከማጋለጥ ሌላ ፋይዳ ያለዉ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም እነዚህ አድርባዮችና ታማኝ ተቃዋሚ የፓርቲ አባላት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በኢትዮጵያ ስላለዉ የዴሞክራሲ ሥርዓት በማዉራት ሕዝባችንን ከማደናገር እንዲቆጠቡ እያሳሰብን ይልቁንም ጊዜዉ ሳይመሽባቸዉ ንስሓ ገብተዉ ከሕዝባችን ትግል ጎን እንዲሰለፉ ምክራችንን ለመለገስ እንወዳለን።

ማንም እንደሚያዉቀዉ እነዚህ የህገወጡ የፓርላማ አባላት እነርሱ እንደሚሉት በመረጣቸዉ ሕዝብ ፈቃድ ፓርላማ የገቡ አይደሉም። ምክር ቤት ለመግባት የተወሰነው ዉሳኔና አገባቡም ከሕዝቡ ግንዛቤ የተሰወረ ግልፅነት የጎደለውና ከፋፋይ እንደሆነ ይህ የደቡብ ኢትዮጵያ ተሓድሶ ኮሚቴ ያምናል። ለምሣሌ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ገና በምርጫዉ ማግስት በአንድ የሕዝብ ልሳን

ስለፓርላማ መግባትና አለመግባት ተጠይቀዉ ሲመሉስ በማያሻማ ሁኔታ "በደምና በላብ ያገኙት ዉጤት" በመሆኑ ፓርላማ እንደሚገቡ ማረጋገጣቸዉ የሚታወስ ነዉ። እንደዕዉነቱ ከሆነ በደምና ላብ የተገኘዉ ውጤት የሚያወላዳም አልነበረም። በአጠቃላይ ከደቡብ ክልል ተገኘ የተባለዉ ድል በካምባታና ሃዲያ ዞን 12 ተወካዮች ብቻ ነበር። እነርሱም ቢሆኑ ፓርላማ የገቡት ከመረጣቸዉ ሕዝብ ጋር መክረዉ ሳይሆን በፕሮፊሰር በየነ ትዕዛዝና አደፋፋሪነት ነው። በአንጻሩ ደግሞ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረትና በደቡብ ህብረት ዓርማ ሥር ወደ ምርጫ ገብተዉ ያገኙትን የሕዝብ ድምፅ በህወሃት/ኢሕአዴግ ተቀምተዉ ተቃዉሞ በማሰማት ላይ የነበሩትን የጌዴኦ ፣ የዳዉሮ ፣ የወላይታ ፣ የደቡብ ኦሞ ፣ የኦሞቲክ ፣ የሲዳማና ሌሎች የደቡብ ህብረት አባል ድርጅቶችን ሳያማክሩና ሳያስወስኑ ፓርላማ መግባታቸዉ ግልፅ ነው። እንዲሁም የኢዴኃህ ምክር ቤትን ውሳኔ ጥሰዉ ፓርላማ የገቡ መሆናቸዉ የሚታወቅ ነዉ። ስለሆነም በወያኔ/ኢሕአዴግ ፓርላማ የገቡ ግለሰቦች ዉሳኔ የኢትዮጵያዊያንን ይሁንታና ፍላጎት ያላገናዘበ ፣ የየድርጅቶቻቸዉንም ዉሳኔ የጣሰ በመሆኑ እነዚህ ግለሰቦች የሚወክሉት ራሳቸዉንና ራሳቸዉን ብቻ መሆኑን ለማስመዝገብ እንወዳለን። ይልቁንም እነዚህ የፓርላማ አባላት ጥፋታቸዉን ተገንዝበው ህጋዊ ካልሆነ ፓርላማ ወጥተዉ የሕዝባችንን ትግል እንዲቀላቀሉ አሁንም ጥሪ እናቀርባለን።

"የተቃዋሚ የፓርላማ አባላት" ተብዬዎቹ ስላስመዘገቡት ዉጤትም ስናገሩ ተሰምተዋል። ዉጤቱ ቀርቶ ሰብእናቸዉን ማስከበር ቢችሉና የአፈ-ጉባኤዉን ግልምጫና ግሳፄ ማስቀረት ከቻሉ ትልቅ ነገር ነዉ። የሕዝብ አጀንዳ አስይዘዉ አስጸድቀዉ ህግ ሆኖ የምናይበት ሁኔታ እንደሌለ ለኛም ለነርሱም ግልፅ ነዉ። ይህስ ይቅር ፣ ለመሆኑ እነዚህ የደቡብን ህዝብ እንወክላለን የሚሉ የፓርላማ አባላት የህወሃት/ኢሕአዴግ ካድሬዎች ራሳቸዉ በቀሰቀሱት ዉዝግብ የአገዛዙ ጦር በጌዴኦ ህዝብ ላይ ዘምቶ ሲገድል ሲያስር ምን የተነፍሱት ነገር አለ? የሲዳማስ ሕዝብ በሕገ መንግስቱ የተሰጠዉን መብቱን በሰለማዊ መንገድ ስለጠየቀ ብቻ ሲዘመትበትና ግፍ ሲፈፀምበት ምን አደረጉ? ምንስ አሉ? የጉራጌ ሕዝብ ለፈለገዉ ሰዉ ድምፁን በመስጠቱ ብቻ ከቤት ንብረቱ እንዲፈናቀል በግፈኞች ሲፈረድበት ምን ተነፈሱ? ይልቁንስ የፕሮፌሰር በየነን በድርጅት ላይ ድርጅት መመስረት ፣ እመራቸዋለሁ በሚሏቸው ድርጅቶች ዉስጥ ቡድናዊና አግላይ አሠራርን ማራመድ ፣ እንዲሁም የሀዲያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን (ሀብዴድን) ደንብ ጥሰው አዲስ መዋቅር መዘርጋታቸዉን በመቃወም ጥያቄ ያነሱ የሀብዴድ አባላትን ማዋከብ ፣ ማንገላታትና ካለዉ መንግሥት ጋር ያለዉን ቀሬበታ በመጠቀም ማሳሰር ነዉ እያየን ያለነዉ። ስለሆነም ስላስመዘገቡት ድልና ዉጤት ዲስኩር ማሰማት መብታቸዉ ሆኖ ፣ በሃድያ ዞን ከሚኖረዉ ቅንና ታጋይ ሕዝባችን እጃቸውን እንዲሰበስቡ ለማስገንዘብ እንወዳለን።

በፕሮፌሰር በየነና መሰሎቻቸው ቂመኛ አስተሳሰብና ከግል ጥቅምና ዝና አርቆ ባለማየት አምባገነኑ መለስና ግብረአበሮቹ ከሞት አፋፍ ድነዉ ዛሬ ለማገገምና መልሶ ለመንሰራራት የሞት ሽረት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። በዉጭ ወዳጆቻቸው ድጋፍና በአገር ከሀዲዎችና አድርባዮች አጋፋሪነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ላይ ዉሃ ለመቸለስ ደፋ ቀና እያሉ ይገኛሉ። በእኛ እምነት መለስና አበሮቹ ተመልሰው እንዲያንሰራሩ መፍቀድ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ስለሚሆን የተቃዋሚ ኃይሎች ራሳቸዉ ተባብረዉና የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተባብረዉ ትግሉን በማፋፋም ይህንን አስከፊ ስርዓት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል። በሰሜን አሜሪካ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ህብረት የተሃድሶ ኮሚቴም በኢትዮጵያ ዉስጥ ለሠላም ፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ እየተደረገ ባለዉ ሕዝባዊ ትግል ጎን በመቆም የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያደርግ መሆኑን በድጋሚ ለማረጋገጥ እንወዳለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

በሰሜን አሜሪካ የደቡብ ህብረት ተሃድሶ ኮሚቴ
ነሓሴ 10 1998